DC PUBLIC CHARTER SCHOOL BOARD

የማሻሻያ አቤቱታ ማሳወቂያ

**የቻርተር ግቦች ፖሊሲ**

ለህዝብ አስተያየት ክፍት የነ

የህዝብ አስተያየት እስከ ኤፕሪል 8፣ 2024 ድረስ ነው የምንቀበለው

**ማጠቃለያ፥** የኮሎምብያ ዲስትሪክት የህዝብ ቻርተር ትምህርት ቤት ቦርድ (DC PCSB) ህዝቡ በቻርተር ግቦች ፖሊሲ ላይ አስተያየቶች የሚሰጥበት እድል ማዘጋጀቱን አሳውቋል። የዲሲ PCSB ሰራተኞች የቻርተር ግቦች ፖሊሲን ማሻሻል ይፈልጋሉ። የታቀዱት ክለሳዎች ነባር የዲሲ PCSB ቻርተር ግቦች ፖሊሲዎችን እና *መመሪያዎችን* በማጠናከር እና በማስፋት አንድ አጠቃላይ ፖሊሲ ለመፍጠር ያለሙ ናቸው[1] በተጨማሪም፣ ክለሳዎቹ 1) ከአመታዊ የት/ቤት አፈፃፀም መረጃ ጠቋሚ ሪፖርት እና ግምገማ (ASPIRE) ፖሊሲ እና ቴክኒካል *መመሪያ* (የዲሲ PCSB የተሻሻለ የተጠያቂነት ስርዓት) እንዲተሳሰሩ ይደረጋሉ እንዲሁም 2) የዲሲ PCSB የ ASPIRE ስርአቱን ተግባራዊ ማድረግ በሚጀምርበት ከ2024 – 25 እስከ 2026 – 27 የትምህርት ዘመን ላይ የግብ ማሳኪያ *መንገዶችን* ያቋቁማሉ። የታቀደው የቻርተር ግቦች ፖሊሲ እና የ ASPIRE ፖሊሲ እና ቴክኒካል *መመሪያ* የDC PCSB የተጠያቂነት ስርዓት ደጋፊ አካላት ነው ያገለግላሉ።

የታቀደው ፖሊሲ እንደሚከተለው በሶስት ክፍሎች የተከፈለ ነው፥

1. ***የቻርተር ግቦችን ማጽደቅ እና ማሻሻል*** DC PCSB አዳዲስ እና የተሻሻሉ ግቦችን በተመለከተ ለመደራደር እና የማጽደቂያ ምክረሀሳብ ለመስጠት የሚጠቀምባቸው *መመሪያዎችን* ይገልጻል። በተለይም፣ ትምህርት ቤቶች ASPIREን እንደ ቻርተር ግቦች ለመውሰድ የሚመርጡበትን ሂደትአካሄድ ያስቀምጣል። በተጨማሪም በተናጠል ድርድር የተደረገባቸው የቻርተር ግቦች እና ከግብ ኢላማዎች፣ ምዘናዎች፣ እና የቢዝነስ ደንቦች የሚጠበቁ ነገሮች በሚመለከቱ ዝቅተኛ መመዘኛ ደረጃዎች ዙርያ የ DC PCSBን አሁናዊ እና የቆየ የአሰራር ልምድ ይሰብስባል።[2] በመጨረሻም፣ የቻርተር ግብ ማሻሻያ ጥያቄዎች የሚስተናገዱበት አሰራር እና የጊዜ ሰሌዳ ተረድቷል፣ እንዲሁም ግቦች የሚወገዱበት ወይም የግቦች ኢላማዎች ዝቅ የሚደረጉበት ሁኔታንም ተገንዝቧል።

2. ***ከ 2022 – 23 እስከ 2026 – 27 ትምህርት ዘመን የግብ ግምገማ*** DC PCSB በተዘረዘሩት የትምህርት ዓመታት በቻርተር ግምገማዎች እና እድሳት ላይ የግብ ስኬትን እንዴት እንደሚገመግም ይገልጻል። በ 2022 - 23 እና 2023 - 24 የትምህርት ውስጥ ግብን ለመወሰን *መመሪያው* ከጁላይ 2023 የቻርተር ግቦች ፖሊሲ እና በየአመቱ ለዓላማ ስኬት በርካታ *መንገዶችን* ያካትታል። [3] ለ 2024 – 25 እና 2025 – 26፣ የትምህርት ዘመን ፖሊሲው ASPIREን እንደ ቻርተር ግቦቻቸው ለመቀበል የመረጡትን ትምህርት ቤቶች ጨምሮ በጊዜ ሂደት የውጤቶች መሻሻልን በምያሳይበት ጊዜ ለሁሉም ትምህርት-ቤቶች የግብ ማሳከያ *መንገዶች* ማቅረቡን ቀጥሏል።

---

[1] የሚከተሉትን ጨምሮ የ DC PCSB ፖሊሲዎች ላይ የተመሰረቱ፣ ወደዚህ ፖሊሲ የተካተቱ በተመለከተ ብዙም ለውጥ የለውም፥ *የኮቪድ-19 ተጽዕኖ ፖሊሲ፣ የPMF ፖሊሲ እና ቴክኒካል መመሪያ፣ PMFን እንደ ቻርተር ግቦች ፖሊሲ ለመውሰድ ይምረጡ፣ የቻርተር ማሻሻያዎች ለተከለሱ ግቦች እና አካዳምያዊ ስኬት ውጤቶች ፖሊሲ፣ እና የASPIRE ፖሊሲ እና ቴክኒካዊ መመሪያ።*

[2] በተናጠል ድርድር የተደረገበት ግብ እድገትን የሚመለከት ነባር *መመሪያ* በዲሲ PCSB ግቦች እና የተማሪ አካዳምያዊ ስኬት ውጤቶች ቻርተር ስምምነት ማሻሻያ ማመልከቻ እና የቻርተር ማመልከቻ *መመሪያዎች* ላይ ሊገኝ ይችላል።

3. ***የቻርተር ግቦች ክትትል እና ለዝቅተኛ አፈጻጸም የሚሰጡ ምላሾች*** የዲሲ PCSB ትምህርት ቤቶችን የቻርተር ግቦችን ለማሟላት የሚያደርጉትን ሂደትለመከታተል የሚከተላቸው አሰራሮችን እና የነ  የአካባቢ ትምህርት ኤጀንሲ (LEA) የቻርተር ግቦቹን በማያሳካበት ጊዜ ሊወሰዱ የሚችሉትን እርምጃዎችን ይገልፃል። የASPIRE ስርአት ላይ የሚታዩ ዝቅተኛ አፈጻጸሞች በተመለከተ ሊወሰዱ የሚችሉ በፖሊሲው ውስጥ ተካትተው የሚገኙ እርምጃዎች በASPIRE ፖሊሲው እና ቴክኒካዊ መመሪያው ላይ የተቀመጡት ስተንዳርዶችን ደግመው የወሰዱ ናቸው።

በ 2024 – 25 ትምህርት ዘመን፣ ዲሲ PCSB የASPIRE ስርዓትን መተግበር ይጀምራል እናም ከሽግግር ግቦች እና ሌሎች ለግብ መሳካት አማራጭ የሚኑ  መንገዶችን ከመጠቀም ይርቃል። ASPIREን እንደ ግቦቻቸው የወሰዱ ትምህርት-ቤቶች ላይ (ወይም የአሁን PMF ትምህርት-ቤቶች ASPIREን ለማካተት እንደምያስቧቸው ግቦች ወይም አዳዲስ በተናጠል ድርድርድ ላይ የተመሰረቱ ግቦች) እና ከ2024 – 25 እስከ 2026 – 27 የትምርት ዘመን ላይ በተናጠል ድርድር ላይ የተመሰረቱ ግቦችን የሚከተሉ ትምህርት-ቤቶች ላይ ተግባራዊ ይደረጉ ዘንድ ዲሲ PCSB ያቀረባቸው የግብ ማሳኪያ መንገዶች የሚመለከት መግለጫ ለማግኘት ከታች ያለውን ሰንጠረዥ ይመልከቱ።

| ት/ቤት አመት | የግብ ስኬትን የሚያሳዩ መንገዶች | |
|---|---|---|
| | ***ASPIRE**ን እንደ ግብ የወሰዱ ትምህርት ቤቶች* | *በተናጠል ድርድር ላይ የተመሰረቱ ግቦች ያሏቸው ትምህርት-ቤቶች* |
| **2024 – 25** | *መንገድ ሀ፥ ደረጃ 3 ወይም ከዚያ በላይ*<br>በASPIRE ደረጃ 3 ወይም ከዚያ በላይ ያግኙ።[4] | *መንገድ ሀ፥ ዒላማዎችን ማሟላት ወይም ማለፍ*<br>በቻርተር ስምምነት ላይ እንደተቀመጠው የግብ ኢላማዎችን ማሟላት ወይም ማለፍ። |
| | *መንገድ ለ፥ መሻሻል*<br>በASPIRE ደረጃ 4 ያገኙ ትምህርት ቤቶች፣ ካለፈው ዓመት ነጥብ ያሻሽሉ።[5] | *መንገድ ለ፥ መሻሻል*<br>ከ 2023 – 24 የትምህርት ዘመን አፈጻጸም ጋር በማነጻጸር የታየውን መሻሻል ይግለጹ። |
| **2025 – 26** | *መንገድ ሀ፥ ደረጃ 3 ወይም ከዚያ በላይ*<br>በASPIRE ደረጃ 3 ወይም ከዚያ በላይ ያግኙ። | *መንገድ ሀ፥ ዒላማዎችን ማሟላት ወይም ማለፍ*<br>በቻርተር ስምምነት ላይ እንደተቀመጠው የግብ ኢላማዎችን ማሟላት ወይም ማለፍ። |

---

[3] አንዳንድ ቋንቋዎች ለግልጽነት እና ትክክለኝነት ሲባል ተከልሰዋል (ለምሳሌ፣ የOSSE ተጠያቂነትን በSTAR ምትክ እና በPARCC ምትክ ደግሞ DC CAPE) እንዲሁም በመንግስት ደረጃ የ MGP ዳታ ባለመኖሩ ምክንያት በ 2023 – 24 ትምህርት ዘመን ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት-ቤቶች የተለየ የእድገት መንገድ እንዲካተት ተደርጓል።

[4] ብዙ የASPIRE ማእቀፎች ላሏቸው ትምህርት-ቤቶች እያንዳንዱ ማእቀፍ በተናጠል እንዲገመገም ይደረጋል።

[5] ዲሲ PCSB የ ትምህርት ዘመን 2023 - 24 የASPIRE ውጤቶችን እና ደረጃዎችን በይፋ አያትምም ነገር ግን ይህንን የግብ ማሳካት መንገድ ብቁ የኑ  ትምህርት-ቤቶች ላይ ተግባራዊ ለማድረግ በግምገማ እና በማደስ ሪፖርቶች ላይ ሊጠቀስ ይችላል።

| ት/ቤት አመት | የግብ ስኬትን የሚያሳዩ መንገዶች | |
|---|---|---|
| | **ASPIRE ን እንደ ግብ የወሰዱ ትምህርት ቤቶች** | **በተናጠል ድርድር ላይ የተመሰረቱ ግቦች ያሏቸው ትምህርት-ቤቶች** |
| | መንገድ ለ (የሚመለከተው በ የዲሲ PCSB ቦርድ የመወሰን ስልጣን)፥ ማሻሻያ[6] በASPIRE ደረጃ 4 ያገኙ ትምህርት ቤቶች፣ ካለፈው ዓመት ነጥብ ያሻሽሉ። | መንገድ ለ (የሚተገበረው በ በዲሲ PCSB ቦርድ የመወሰን ስልጣን መሰረት ነው፥ ማሻሻያ[7] ሙሉበሙሉ ያልተሟሉ የግብ ኢላማዎችን በተመለከተ፣ ከ 2024 – 25 የትምህርት ዘመን አፈጻጸም ጋር በማነጻጸር የታየውን መሻሻል ይግለጹ። |
| **2026 – 27** | ደረጃ 3 ወይም ከዚያ በላይ በASPIRE ያግኙ። | የቻርተር ስምምነቱ ላይ የተቀመጡ የግብ ኢላማዎችን ያሳኩ ወይም ይለፉ። |

**ህዝባዊ ስብሰባዎች፥** ህዝባዊ የህዝብ አስተያየት የሚሰማበት ስብሰባ ኤፕሪል 8፣ 2024 ከቀኑ 6፡00 ሰዓት ይካሄዳል። ድምጽ የሚሰጥበት ጊዜ ጁን 10፣ 2024 ከቀኑ 6:00 ሰዓት ይናል። እባክዎ ለመመዝገብ www.dcpcsb.org/events ይጎብኙ።

**የህዝብ አስተያየት መመሪያዎች፥** አስተያየቶች ከኤፕሪል 8 ቀን 2024 በፊት ወይም በዚሁ ቀን መቅረብ አለባቸው።[8] ከሚከተሉት ዘዴዎች አንዱን በመጠቀም በ"ASPIRE ፖሊሲ እና ቴክኒካል መመሪያ - የሀሳቤ ይካተትልኝ አቤቱታ ሰነድ" የተለዩ አስተያየቶችን ማስገባት ይችላሉ።

1. ወደ https://dcpcsb.org/public-comment በመሄድ በሕዝብ ተሳትፎ ስብሰባው ላይ ማስረጃዎትን ለማቅረብ ይመዝገቡ። ቅጹን ለመሙላት "በስብሰባ ላይ ለመመስከር ይመዝገቡ" የሚለውን ትር ጠቅ ያድርጉ። ለመመስከር የመመዝገቢያ ቀነ-ገደብ ኤፕሪል 8፣ 2024 እኩለ ቀን ነው።
2. የጽሁፍ አስተያየት በሚከተለው አማካኝነት ያስረክቡ፥
   a. የኦንላይ ቅጽ በ https://dcpcsb.org/public-comment
   b. በፖስታ መልእክት፣ በአካል ይዞ መምጣት ወይም በመልእክተኛ፥ ትኩረት፥ የሕዝብ አስተያየት፣ የዲሲ የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤት ቦርድ፣ 3333 14th Street NW፣ Suite 210፣ ዋሽንግተን ዲሲ 20010።

   እባክዎን ዲሲ PCSB የጽሑፍ አስተያየቶችን የሚቀበለው ከህዝባዊ ስብሰባው አንድ ቀን በፊት ከቀኑ 11፡ 59 በፊት ወይም በዚሁ ሰአት እንደነ ልብ ይበሉ።
3. የድምጽ ምስክርነት በስልክ ያቅርቡ፥ በ (202) 328-2660 ይደውሉ እና አማራጭ 2ን ይምረጡ። ምስክርነትዎን ለመቅረጽ እስከ አምስት ደቂቃ ድረስ ይኖሮታል። እባክዎ ሁሉም አስተያየቶች ወደ ጽሑፍ እንደሚቀየሩ እና ለህዝብ እንደሚደርሱ ልብ ይበሉ።

---

[6] የዲሲ PCSB ቦርድ ተቀባይነት ያለው ማሻሻያ ሲወስን በዋናነት የተማሪ ቡድንን፣ የማዕቀፍ ምድብ እና የቡድን አፈጻጸምን ይመለከታል።

[7] የዲሲ PCSB ቦርድ ተቀባይነት ያለው ማሻሻያ ሲወስን በዋናነት በትምህርት ቤት እድገት እና በትምህርት ቤት ስኬት ግቦች ላይ እንዲሁም በክፍለ ሃገር እና በሴክተሩ አፈጻጸም ላይ የታዩ መሻሻሎችን በተመሳሳይ መመዘኛ መስፈርት ያያል።

[8] ዲሲ PCSB ሙብቱ የተጠበቀ ነው፣ ነገር ግን የተላከለት ይዘት በከፊል ወይም በሙሉ ብልግናዊ አገላለጾችን ያካተተ በመኑ ለህትመት አይበቃም ብሎ ባመነ ጊዜ ይዘቱን የመገምገም፣ አስቀድሞ የማየት፣ የማጣራት፣ የማረም፣ ውድቅ የማድረግ፣ ወይም የማስወገድ ግዴታ ግን የለበትም።

**ለበለጠ መረጃ፡ የሚከተለውን ያናግሩ፥** Starling Temp፣ ስፔሻሊስት፣ የትምህርት ቤት አፈጻጸም መምሪያ፣ በ stemp@dcpcsb.org ወይም (202) 277-2731።